## የወላጅ እና የቤተሰብ
## ተሳትፎ ፖሊሲ

የዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ይኸን የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ እንዲሻሻል አድርጎል ከትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ከህብረተሰቡ አባላት እና ከወላጆች በ10/12/2020 ጋር በመነጋገር ከዚያም በ20-21 የWRES የታይትል I የምሽት ፕሮግራም እለት ወላጆች እንዲመለከቱት ተደርጎል። ይህ ፖሊሲ ለአካባቢው ማህበረሰብ በድረገፅ እና በዜና መፅሔት እንዲዳረስ ይደረጋል። ልጆቻቸው በፕሮግራሙ ተሳታፊ ለሆኑ ወላጆች የተዘጋጀው የታይትል I እቅድ አጥጋቢ ካልሆነ የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች የእቅዱን ማመልከቻ ለስቴቱ በሚላክበት ወቅት የወላጆችን አስተያየት አብሮ ይላካል። የዚህ የወላጆች ተሳትፎ እቅድ ተለዋዋጭ የሆነውን የወላጆችና የትምህርት ቤት ፍላጎት ለማሟላት በየዓመቱ እንዲሻሻል ይደረጋል።

**የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎችን በሚካሄድበት ወቅት የዚህ ስምምነት መሰረት የእያንዳንዱ ልጅ የግል የአካዳሚ ውጤት በተመለከተ ውይይት ይካሄዳል።** የዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች በኖቬምበር 11፣ 12 እና 13 2020 እና ፌብሩዋሪ 18-19፣ 2021.ይካሄዳል። አሳሳቢ ወይም አስፈላጊ ጉዳይ ካለ ጉባኤዎች በማንኛውም ጊዜ ወላጅ ወይም አስተማሪ ሲጠይቅ ይካሄዳል።

**የሪፖርት ካርድ ወደ ቤት በሚከተሉት ቀናት ይላካል፤** ኖቬምበር 13፣ ፌብሩዋሪ 19፣ ኤፕሪል 23 እና ጁን 21 ቀን።

## የወላጅ እና የቤተሰብ
## ተሳትፎ ፖሊሲ ቀጣይ

በወላጆች ጥያቄ መሰረት በኢሜል፣ በየቀኑ የት/ቤት-ቤት ማስታወሻ መላኪያ፣ በማስታወሻ እና ቴክስት መልክቶች እና/ወይም በስልክ በመደወል የልጆቻቸውን ውጤት የሚያሳይ ሪፖርቶች ሊላክ ይችላል።
**ወላጆች ከሰራተኞች ጋር በቀላሉ እንዲገናኙ ማስቻል።** በተለይም ሰራተኞች በሚከተለው ሁኔታ ከወላጆች ጋር ለመመካከር ዝግጁ ናቸው፤ ወላጆች በትምህርት ቤት አስተማሪዋችን በስልክ ጥሪ፣ ማስታወሻ ወይም በኢሜል በመላክ ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም በፎል እና ስፕሪንግ ወቅት ቀጠሮ በመያዝ የስብሰባ ጊዜ በመወሰን መገናኛት ይቻላል። ወላጆች ከአስተማሪዋች ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት ከመደበኛ ትምህርት በፊት፣ እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት እና ከትምህርት በኋላ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። አስተማሪዋች በተቻለ መጠን ወላጆች በሚናገሩት ቋንቋ ለማነጋገር ያላቸውን ድጋፍ ሪሶዋርስ ይጠቀማሉ።

**ለወላጆች የበጎ ፈቃደኝነት እድል እንዲያገኙ በልጆች ክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ እና የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዋችን እንዲመለከቱ የሚከተለውን ያደርጋሉ፤** ወላጆች በማንኛውም ጊዜ ልጆቻቸውን በክፍል ውስጥ እንዳሉ ለመመልከት እና በበጎ ፈቃደኝነት ለመሳተፍ አስተማሪዋችን መጠየቅ ይችላሉ። ወላጆች የበጎ ፈቃደኛ መታወቂያ (ባጅ) ፈቃድ ካገኙ በኋላ መሳተፍ ይችላሉ። በበጎ ፈቃደኞነት ለማገልገል እባክዎን ከትምህርት ቤቱ ጋር ይገናኙ።

**በኦንላይን እዚህ ይመዝገቡ፡**

**http://bit.ly/signWRcompact2021**


ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

5700 Sanger Avenue,
Alexandria, VA 22311
(703) 824-6950
www.acps.kl2.va.us/ramsay/


# ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ እና የወላጅ እና የትምህርት ቤት ስምምነት

**ተልእኮ፤** *የዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዋች በባህል ብቃት ያላቸው፣ በራሳቸው ሃይል የተሞሉ እና የህይወት ዘመን ተማሪ በመሆን ለውጤታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።*

**እይታ፤** *በዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ያለን ቡድን ጠንካራ ግንኙንት እና የተሟላ ልጆችን ለመፍጠር ቁርጠኝነት ያላቸው ውጤታማ በሆነ ትብብር ሁሉን አቀፍ በሆነ የትምህርት ከባቢያዊ ሁኔታ እውቀት በእውነተኛ አለም በስራ በማዋል ተማሪዋቻችንን ለዓለምአቀፍ ውጤታማነት ማብቃት።*

**እምነታችን ፤** *በመረጥነው መንገዳችን ለውጤታማነት መጎዝ!*

## የትምህርት ቤቱ ኀላፊነቶች

ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚከተሉትን ይፈፅማል፤ ጥራት ያለው ሥርዓተ-ትምህርት እና ትምህርት ይሰጣል ድጋፍ ሰጪ እና ተገቢው የትምህርት ከባቢ ሁኔታ የተሟላበት በመፍጠር
ተሳታፊ የሆኑ ልጆች የስቴቱን የአካዳሚ ደረጃ መመዘኛ እንዲያሟሉ ለማስቻል የሚከተለውን ማከናወን፤

- በክፍል ውስጥ የሚያጎጎና የመማር ፍሎጎት የሚቀሰቅስ የትምህርት ልምድ ማቅረብ፣
- ለእያንዳንዱ ተማሪ ተስማሚ የሆኑ ቴክኒክ እና ማቴሪያሎች በመመምረጥ መጠቀም፣
- ከተማሪዎች የሚጠበቀው ከፍተኛ የትምህርት ውጤት እንዲሆን ማድረግ፤ የሥርዓተ-ትምህርቱን እና የማስተማር ሂደቱን በሚያስፈልገው ልዩ ልዩ እቃዎች ሞሟላት ።

### የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቶች

ተማሪዎች ማንነታቸውን እና ከእነሱ ዓለም ጋር እንዴት እንደሚገናኙ በሚገልፅ መልኩ ያስባሉ፣ ያነባሉ፣ ይፅፋሉ፣ ያዳምጣሉ እና ይናገራሉ። አስተማሪዎች እንዴት ንባብና ፅሁፍን ለመዝናኛ ፣ ለመገናኛ እና ትርጉም ላለው ራስን ለመግለፅ እንዲችሉ ተማሪዎችን ያግዛሉ።

### ሳይንስ

ተማሪዎች ማስረጃዎችን በመፍጠር እና መጠቀም የሣይንስ መግለጫዎችን ይፈጥራሉ፣ ጥራት ያሳድጋሉ እና በስራ እንዲውል ያደርጋሉ።

### ሙዚቃ ኢንኮር

- ሥነ ጥበብ(አርት) ትምህርት የምስክር ወረቀት ባለው የአርት አስተማሪ በሳምንት አንድ ቀን ይሰጣል።
- የድምፅ ሙዚቃ ትምህርት ምስክር ወረቀት ባለው የሙዚቃ አስተማሪ በሳምንት አንድ ቀን ይሰጣል።
- የመሳሪያ ሙዚቃ ትምህርት ከአራተኛ ክፍል ይጀምራል።
- የስፖርት ትምህርት ምስክር ወረቀት ባለው የስፖርት አስተማሪ በሳምንት ሁለት ቀናት ይሰጣል።
- ቤተ-መፅሀፍት የምስክር ወረቀት ባለው ባለሞያ በሳምንት አንድ ቀን ይዘጋጃል።

### ሂሳብ ትምህርት

ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው ቁጥሮችን በመረዳት እና ሂሳብ ስሌት፣ ልኬት፣ ጂኦሜትሪ፣ አልጅብራ እና የመረጃ ትንተና እና ፕሮባቢሊቲ ትምህርት ላይ ያተኩራሉ።

### ማህበራዊ ጥናቶች

የሲቪክ እሳቤ ያላቸውን ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር እንጥራለን። የአገራችንን ወደፊት ማንነት ለመቅረፅ ሁሉም ተማሪዎች የብሄራዊ ቅርሶችን እንዲረዱ ይደረጋል ። ተማሪዎች የጂኦግራፊ መሳሪያዎች መጠቀም ታሪካዊ ክስተቶችን፣ ህዝቦችን፣ ቦታዎችን እንዴት እንደሚተነተኑ እና እንደሚተረጉሙ እንዲማሩ ይደረጋል።

### ልዩ ፕሮግራሞች

- ለልዩ ችሎታ እና ስጦታ (TAG) ፕሮግራም ካሉበት የክፍል ደረጃ የአካዳሚ ብቃት በላይ ለሆኑ ልጆች ይሰጣል።
- የቤተሰብ ህይወት ትምህርት እንደ እድሚ ደረጃቸው ይሰጣል።
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቶች ይሰጣል።
- የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ይሰጣል።

## በቨርችዋል + የትምህርት ቤቱ ኀላፊነቶች

**በቨርችዋል የትምህርት ከባባቢ ሁኔታ ዊሊያም ራምሲ (WRES) የሚከተሉትን ያከናውናል፤**

- በቨርችዋል የትምህርት ሁኔታ ተማሪዎች የሚያገኙትን ውጤት በየጊዜው ማሳወቅ፣
- ቤተሰቦችን በትምህርት እንዲሳተፉ አስፈላጊው ሪሶዋርስ ድጋፍ እንዲያገኙ ማገዝ ፣
- ቤተሰቦች የቴክኒክ ድጋፍ/ አስፈላጊ ሲሆን ስልጠና እንዲያገኙ ማገዝ ፣
- ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነት እድል እንዲገኙ ማስቻል።

## የቤተሰብ ኀላፊነቶች

**የሚከተሉትን በማከናውን የልጄ የአካዳሚ ውጤታማ ለማድረግ ንቁ ተሳታፊ እሆናለሁ፤**

- በየቀኑ ከልጄ ጋር የትምህርት ቤት ውሎውን በመወያየት፣
- የልጄን ትምህርት በመከታተል በመቆጣጣር፣
- የልጄን የቤት ስራ ማጠናቀቁን በማረጋገጥ፣
- ለልጄ ድጋፍ በማድረግ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኝ በመፈለግ፣
- ከትምህርት ውጭ የሆነ ልጄ በኮምፒወተር መስታወት ፊት የሚያጠፋው ግዜ መገደብ ፣ የሚመለከተውን ቪዲዬ፣ ድረገፅ፣ እና ሙዚቃ መቆጣጠር።
- ማበረታቻ እና ማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ወደ ቤት በሚላከው የባህሪ ሪፓርት መሰረት።

**የሚከተሉትን በማከናውን በልጄ የትምህርት ቤት ንቁ ተሳታፊ እሆናለሁ ፤**

- በበጎ ፈቃደኛነት በማገልገል በምችልበት ሰዓት፣
- በልጄ ትምህርት በተመለከተ ውሳኔ አሰጣጥ ተሳታፊ በመሆን፣
- ወርክሸፕ እና የት/ቤት ፕሮግራም በመሳተፍ በምችል ወቅት፣
- በትምህርት ቤት እና/ወይም በትምህርት ቤት ዲስትሪክት የወላጅ አማካሪ ቡድን አባል በመሆን፣
- የቲዊተር፣ ፊስቡክ፣ ኢንስትግራም ወይም ድረገፅ acps.k12.va.us በመጠቀም ስለልጄ ትምህርት ቤት ወቅታዊ መረጃ ማግኘት።
- የልጄን ቦርሳ በየእለቱ በመመለከት እና በጊዜው የተላኩ ቅፆችን መመለስ።

## በቨርችዋል + የቤተሰብ ኀላፊነቶች

- ተማሪው በሰዓቱ ከእንቅልፉ እንዲነሳ፣ ልብሱን እንዲለብስ ፣ ቁርስ እንዲበላ እና በሰዓቱ ዙም በመክፈት እንዲጠባበቅ ማድረግ፣
- ለተማሪው ፀጥታ የሰፈነበት የመማሪያ ቦታ ማዘጋጀት እና የሚረብሹ ነገሮችን ማስወገድ፣
- በቀጥታ ትምህርት በሚካሄድበት ሰዓት ተማሪውን ሌላ ስራ እንዲያግዝ ከመጠየቅ መቆጠብ፣
- ተማሪውን ከሚፈለገው በላይ አለማገዝ - የአካዳሚ ሙከራ እንዲያደርጉ ማበረታታት እና ከስህተቱ እንዲማር ማድረግ።

## የተማሪ ኀላፊነቶች

**የሚከተሉትን በማከናውን በራሴ የትምህርት ውጤታማ ለመሆን ንቁ ተሳታፊ እሆናለሁ ፤**

- የትምህርት ቤት ውሎየን ከወላጅ/ አሳዳጊ ጋር በየቀኑ መወያየት፣
በየቀኑ በትምህርት ላይ መገኘት፣
በየቀኑ ቢያንስ 8-10 ሰዓታት እንቅልፍ ማግኘት፣
ሁሉንም የትምህርት ቤት እቃዎች በመያዝ ለመማር ዝግጁ መሆን።
በየቀኑ የቤት ስራየን ማጠናቀቅ፣
እርዳታ ሲያስፈልገኝ መጠየቅ፣
በየእለቱ ምሽት በቤት ውስጥ ቢያንስ 30 ደቂቃዎች ማንበብ፣
በየእለቱ ምሽት በቤት ውስጥ ፅሁፍ መለማመድ፣ በደብተሬ ወይም በጆርናል ላይ በየቀኑ ፅሁፍ መለማመድ።
ዲጂታል ዜግነት(Digital Citizenship) ደንቦችን በት/ቤት እና በቤትም ውስጥ መከተል።
የሞባይል ስልኬን፣ ኮምፒውተር ወይም ታብሌት በተገቢው መንገድ መጠቀም፣
ለራሴ፣ ለሌሎች ተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለጎብኝዎችም ክብር መስጠት፣
ከትምህርት ቤት የሚሰጥ ሁሉንም መረጃ እና ቅፃች በየቀኑ ለወላጅ/ አሳዳጊ መስጠት፣
የአካዳሚ የትምህርት ውጤት ለውጥ መከታተል እና በክፍል ውስጥ እኔ እና አስተማሪዮ ያስቀመጥናቸውን ግቦች ውጤት ለማግኘት መጣር

**በቨርችዋል ትምህርት።**

- በየቀኑ በሰዓቱ የኮምፒውተር መገናኘት ካሜራውን ክፍት በማድረግ፣
- የሲንክሮኒየስ እና አሲንክሮኒየስ ትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ማወቅ እና የሚጠበቁ ስራዎችን ማወቅ፣
- እኔ ለምገለገልበት ቴክኒዋሎጂ ኀላፊነት መውሰድ እና በማይሰራበት ወቅት እርዳታ መጠይቅ።